የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፱

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33rd Year No. 4
ADDIS ABABA, 28th October, 2026

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ፲፱
የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ ደንብ.....ገጽ ፳ሺ፫፻፲፮

Content

Regulation No. 597/2026
A Regulation to further amend Federal Income Tax (Amendment) Regulation .....Page 20316

ደንብ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ፲፱

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን እንደገና ለማሻሻል የወጣ ደንብ

ግልጽነትን እና አስተዳደራዊ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፷፱/፪ሺ፷ (እንደተሻሻለ) ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፭፻፸፫/፪ሺ፲፱ (እንደተሻሻለ) እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፷፱/፪ሺ፷ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፩፻፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ ደንብ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ፲፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ማሻሻያ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፬፻፲/፪ሺ፱ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፦

REGULATION NO. 597/2026

A REGULATION ISSUED TO FURTHER AMEND THE COUNCIL OF MINISTERS FEDERAL INCOME TAX REGULATION

WHEREAS, it has become necessary to further amend the Council of Ministers Income Tax Regulation No. 410/2017 (as amended) to ensure clarity, administrative efficiency, and alignment with the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended);

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 104 Sub Article (1) of the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended), the Council of Ministers hereby issues the following Regulation.

1. Short Title

This Regulation may be cited as "A Regulation to further amend Federal Income Tax (Amendment) Regulation No. 597/2026".

2. Amendment

The Council of Ministers Income Tax Regulation No. 410/2017 (as amended) is further amended as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩) የደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩."አዋጅ" ማለት የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ (እንደተሻሻለ) ነው፡፡"

፪) ከደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል፣ ከንዑስ አንቀጽ (፪) ጀምሮ ያሉት ንዑስ አንቀጾች ተሸጋሽገዋል፡፡"

"፪/ "ለዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያ የሚያመቻች የኦንላይን መድረክ" ማለት አንድ ሰው የዲጂታል ይዘት እንዲፈጥር፣ እንዲጭን፣ እንዲያትም፣ እንዲያሰራጭ፣ በቀጥታ እንዲያስተላልፍ፣ እንዲያስተዋውቅ ወይም በሌላ ማናቸውም ዘዴ ለተጠቃሚዎች እንዲያደርስ የሚያስችል ድረ ገጽ፣ መተግበሪያ፣ የኤሌክትሮኒክስ የመገበያያ ቦታ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት፣ የቀጥታ ስርጭት አገልግሎት ወይም ሌላ የዲጂታል መድረክ ሲሆን፣ የዲጂታል ይዘት ፈጣሪው ላከናወነው ተግባር፡-

ሀ) ክፍያ የሚፈጽም ወይም ክሬዲት የሚያደርግ፣

ለ) በዲጂታል ይዘት ፈጣሪው ስም ክፍያ የሚሰበስብ፣የሚቀበል፣የሚቆጣጠር ወይም ክፍያ እንዲፈጸም የሚያመቻች፣ ወይም

ሐ) የዲጂታል ይዘት ፈጣሪው ከማስታወቂያ፣ ከአባልነት መዋጮ፣ ከስፖንሰርሺፕ፣ ከሮያልቲ፣ ከጉርሻ፣ ከእርዳታ፣ከኮሚሽን፣ ከሽያጭ፣ ከፈቃድ ወይም ከማናቸውም የዲጂታል ይዘትን ወደ ገንዘብ የመለወጥ ተግባር የሚያገኘውን ክፍያ የሚወስን፣ የሚያሰላ፣ ወይም ሪፖርት የሚያደርግ ነው።"

1) Sub-article (1) of Article 2 of the Regulation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1. **"Proclamation"** means the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016 (as amended)."

2) Following Sub-Article (1) of Article 2 of the Regulation, the following new Sub-Article (2) is added; and the subsequent sub-articles from Sub-Article (2) onwards are renumbered accordingly.

"2/ **"Online platform facilitating payment for digital content creators"** means any website, application, electronic marketplace, social-media service, live-streaming service, or other digital platform that enables a person to create, upload, publish, distribute, stream, promote, or through any other means deliver digital content to users, and which, in respect of the activity performed by the digital content creator:

a) executes payment or extends credit;

b) collects, receives, manages, or facilitates payment on behalf of the digital content creator; or

c) Determines, calculates, or reports earnings derived by the digital content creator from advertising, membership fees, sponsorship, royalties, tips /bonuses, donations, commissions, sales, licensing, or any other form of digital content monetization."

CamScanner

፫) የደንቡ አንቀጽ ፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፬ ተተክቷል፦

"፬. <u>በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት</u>

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ዓላማ ማንኛውም ሰው ከ፺፩ ቀን በላይ መቆየቱን ለመወሰን የዚህ ሰው ወይም ግንኙነት ያለው ሰው ተያያዥ ፕሮጀክት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት።

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተን ማንኛውም ግንባታ፣ ፕሮጀክት ወይም ተያያዥ ስራ የሚያከናውን ሰው ከ፺፩ ቀናት የሚበልጥ የቆይታ ጊዜ ማሟላቱን ለመወሰን፤ ግንኙነት ባለው ሰው የተከናወነ ማንኛውም ግንባታ፣ ፕሮጀክት ወይም ተያያዥ ስራ መጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ያከናወነው ስራ በወሰደው ጊዜ ላይ ተጨምሮ መሰላት አለበት።

፫/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው መሰረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውስጥ የሚያገኘው ገቢ ግብር ይከፈልበታል።

፬) የደንቡ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) ተተክቷል፦

"፯(፩) (ሐ) ከወር ጋር በተገናኘ **"የገበያ የማበደሪያ ወለድ"** መጣኔ ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው የሚወስነው የፖሊሲ የወለድ መጣኔ ነው።"

3) Article 4 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 4:

"4. <u>Permanent Establishment</u>

1/ In determining whether a person exceeds the 91 days period specified in Article 4 Sub-Article (2) Paragraph (c) of the Proclamation, account shall be taken of a connected project of the person or of a related person.

2/ When a person operates a building site or conducts a project or activity referred to in Article 4 Sub-Article (3) of the Proclamation, any connected activities conducted by a related person shall be added to the period of time during which the first-mentioned person has operated the building site or conducted the project or activities for the purpose of determining whether the 91 day period exceeded.

3/ Without prejudice to the provisions of this Article, and in accordance with the provisions of Article 7 Sub-Article (2) of the Proclamation, a non-resident shall be liable to pay tax on income derived from sources in Ethiopia.

4) Article 7 Sub-Article (1) paragraph (c) is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1) paragraph (c):

"7 Sub-Article (1) paragraph (c) "**market lending rate**" in relation to a month means the Policy Interest Rate determined from time to time by the National Bank of Ethiopia."

CamScanner

፭) ከደንቡ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል፤ አዲስ ንዑስ አንቀጽ በመጨመሩ ምክንያት ከንዑስ አንቀጽ (፪) ጀምሮ እስከ ንዑስ (፬) ያሉት ከንዑስ አንቀጽ (፫) እስከ (፭) በመሆን ተሸጋሽገዋል፤

"፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፺፰ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከራስ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ ስለመያዝ የተደነገገው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በዲጂታል ወይም በሌሎች ማናቸውም መንገድ በፍሪላንስ ወይም ከርቀት በሚከናወን የሥራ ዘዴ የሚያገኘውን ገቢ ይጨምራል።"

5) The following new Sub Article (2) is added after Sub-Article (1) of Article 20 and former Sub-Articles (2) to (4) are renumbered (3) to (5):

"2/ The provisions of Article 98 of the Proclamation and Sub-Article (1) of this Article applies to income derived by a resident from digital or from any type of freelance services or income from businesses carried out through remote services."

፮) ከደንቡ አንቀጽ ፳፯ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፯ ተጨምሯል፤ የቀድሞው አንቀጽ ፳፯ አንቀጽ ፳፰ በሚል ተሸጋሽጓል: -

"፳፯. <u>የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ኪራይ ገቢ ግብር</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ንዑስ አንቀጽ (፭) ተፈጻሚ የሚሆነው የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ለሌለባቸው የሰንጠረዥ "ለ" ግብር ከፋዮች ብቻ ስለሆነ የደረጃ "ለ" የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ከፋዮች ግብር በአዋጁ አንቀጽ ፶ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የሚከፈል ይሆናል።"

6) The following new Article 27 is added after Article 26 of the Regulations. The previous Article 27 is renumbered as Article 28:

"27. <u>Rental Income Tax of Category "B"</u> <u>Taxpayers</u>

Article 15 Sub-Article (5) of the Proclamation applies only to Schedule "B" taxpayers who do not have the obligation to maintain books of account. Accordingly, Category B" rental income taxpayers shall pay the tax in accordance with Article 50 Sub-Article (3) of the Proclamation."

፯) ከደንቡ አንቀጽ ፴፩ በተሸጋሸገው አንቀጽ ፴፮ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፴፯ እና ፴፰ ተጨምረዋል፤ የነባሩ ደንብ አንቀጽ ፴፮ አንቀጽ ፴፱ በመሆን ተሸጋሽጓል፤

7) The following new Articles 37 and 38 are added after Article 35 or the renumbered Article 36 of the Regulation; the existing Article 36 of the Regulation is hereby renumbered as Article 39.

CamScanner

"፴፯. <u>የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ</u>

፩/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እና የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተደነገገው መሰረት በድርጅት ደረጃ ግብር የመክፈል ግዴታ የሌለባቸው ቢሆንም ከአባሎቻቸው ሰብስበው ገቢ ለሚያደርጉት ግብር አፈጻጸም የሂሳብ መዝገብ የመያዝ እና ይህንን የሂሳብ መዝገብ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ለታክሱ ባለስልጣን ማቅረብ አለባቸው።

፪/ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድን በተመለከተ በአዋጁ የተመላከተውን አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል።

፴፰. <u>የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮች</u>

የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮች ሊከፍሉት የሚገባው ግብር በግምት የሚወሰነው የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል።"

፫) ከደንቡ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ (፬) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል።

"፭/ ከስምንት መቀመጫ በታች ላላቸው ተሽከርካሪዎች የሚፈቀደው የእርጅና ቅናሽ መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ገደብ ይደረግበታል።"

"37. <u>Obligation to Maintain Books of Account</u>

1/ Limited Liability Partnership and Collective Investment Funds, though they have no tax obligation at a body level based on Article 19(3) of the Proclamation, shall maintain books of account and submit them to the Tax Authority at the end of the tax year for the administration of the tax withheld from, and remitted on behalf of, their members"

2/ The Ministry may issue a Directive determining the application of the Proclamation to collective investment funds.

"38. <u>Taxpayers who Fail to Maintain Books of Account</u>

The tax liability of taxpayers who fail to maintain books of account shall be determined by an estimation in accordance with the Directive to be issued by the Tax Authority."

8) The following new Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) of Article 36 or Sub-Article (4) of the renumbered Article 39 of the Regulation:

"5/ The amount of depreciation allowance permitted for vehicles with less than eight seats shall be subject to a limit to be determined by a directive to be issued by the Ministry."

CamScanner

፱) የደንቡ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፪)ፊደል ተራ (ሀ) ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል፡-

፵፯ ንዑስ አንቀጽ "(፪) ፊደል ተራ (ሀ) ኪሣራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ከሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ከሆነ ኪሣራው በሚቀጥሉት ፲ (አስር) ዓመታት ውስጥ በእኩል መጠን ተከፋፍሎ በየግብር ዓመቱ በወጪነት ይያዛል፤"

፲) የደንቡ አንቀጽ ፵፰ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፵፰ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፰ ተተክቷል፡-

"፵፰. <u>የባንኮች ኪሳራ መጠባበቂያ</u>

፩/ ማንኛውም ባንክ በአንድ የግብር ዓመት ለኪሳራ የያዘው የመጠባበቂያ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ በተቀመጠ የጥንቃቄ መስፈርት መሰረት የተሰላ መሆኑ ከተረጋገጠ በግብር ዓመቱ የመጠባበቂያ ሂሳቡ መጠን ፹% (ሰማንያ በመቶ) በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ተቀናሽ የሚሆነው የመጠባበቂያ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የሚወሰነውን የባንኩን የስጋት ደረጃ መሰረት የሚያደርግ ሆኖ ከባንኩ ካፒታል ፩፻% የሚበልጥ ሊሆን አይችልም።

9) Article 44 Sub-Article (2) of Paragraph (a) or as renumbered Article 47 Sub-Article (2) Paragraph (a) of the Regulation is hereby deleted and replaced by the following new Article 47 Sub-Article (2) Paragraph (a):

"47 Sub-Article (2) Paragraph (a) Where the loss is related to business operations other than those specified in paragraph (a) of this Sub-Article (1) this Article, such loss shall be apportioned equally and deducted as an expense in each of the subsequent 10 (ten) years;"

10) Article 45 or the renumbered Article 48 of the Regulation is deleted and replaced by the following Article 48:

"48. <u>Loss Reserve of Banks</u>

1/ Banks shall be allowed for 80% (eighty percent) of their loss reserve made in a tax year as deductible expense, provided that the amount of loss reserve has been calculated in accordance with the prudential requirements prescribed by the National Bank of Ethiopia.

2/ The reserve deductible under this Article shall be determined based on the risk level of the bank as determined by the directives of the National Bank of Ethiopia; provided, however, that it shall not exceed 100% of the bank's capital.

CamScanner

፲፩) የደንቡ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍል ሰባት ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ ክፍል ሰባት ተተክቷል፦

"ንዑስ ክፍል ሰባት

የግብር ከፋዮች ደረጃ

"፶፪. **የግብር ከፋይ ደረጃ አወሳሰን**

የግብር ከፋይ ደረጃ የሚወሰነው እንደሁኔታው ግብር ከፋዩ በተሰማራበት በሰንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" የግብር ማስከፈያ ሰንጠረገሮች ስር የሚወድቀውን የግብር ከፋዩን አመታዊ ጠቅላላ ገቢ መሰረት በማድረግ ይሆናል።

፶፫. **የግብር ከፋዮች አመዳደብ**

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የግብር ከፋዮች ምደባ የሚከናወነው በእያንዳንዱ የግብር አመት በተናጠል ሲሆን፤ ምደባው ሳይለወጥ ለግብር ዓመቱ ሙሉ የሚያገለግል ይሆናል።

፪/ በአንድ የግብር አመት ውስጥ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ሆኖ የተመደበ ግብር ከፋይ ከዚያ በኋላ ባሉት የወደፊት አመታት ሁሉ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ሆኖ ይቀጥላል።

፫/ አንድ ግብር ከፋይ በአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የደረጃ "ሀ" ወይም "ለ" ግብር ከፋይ ሆኖ እንዲመደብ ለማድረግ የሚያስችለው የግብር ከፋዩ አመታዊ ጠቅላላ ገቢ በግብር አመቱ ውስጥ ከሰንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ያገኘው ጠቅላላ ገቢ ነው።

11) Sub-Section seven of Section Five of the Regulations is deleted and replaced by the following new Sub-Section Seven:

"Sub Section Seven

Category of Taxpayers

52. Determination of Taxpayer Category

The taxpayer category shall be determined based on the taxpayer's annual gross income falling under tax Schedules 'B' and 'C', as the case may be, in which the taxpayer is engaged.

53. Categorization of Taxpayers

1/ Subject to Sub-Article (2) of this Article, the determination of a taxpayer's tax category under Sub-Article (1) of Article 3 of the Proclamation shall be made separately for each tax year and shall apply for the whole of the tax year without making a change.

2/ A taxpayer who is determined to be a Category "A" taxpayer for a tax year shall remain a Category "A" taxpayer for all future tax years.

3/ For the purposes of determining whether a taxpayer is Category "A" or "B" taxpayer for a tax year under Sub-Article (1) of Article 3 of the Proclamation, the annual turnover of a taxpayer is the gross income of the taxpayer for a year from Schedule "B" and "C".

CamScanner

፬/ ለግብር ዓመቱ የሚታሰበው የግብር ከፋዩ አመታዊ ጠቅላላ ገቢ ግብር የሚከፈልበትን እና ከግብር ነጻ የሆነ ገቢን ይጨምራል።

፭/ በዚህ ደንብ ውስጥ ስለደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የተደነገገው የአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ይጨምራል።

፶፬. <u>የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ</u>

፩/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች አመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ የሚወሰነው የታክሱ ባለስልጣን በየሶስት ዓመቱ በሚያደርገው የገበያ ጥናት ይሆናል።

፪/ የታክሱ ባለስልጣን የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የሚያወጣውን ለንግድ ዘርፉ አግባብነት ያለውን ጥቅል ዋጋ ግሽበት መረጃ መሰረት በማድረግ በየሦስት ዓመቱ የሚከናወነው የገበያ ጥናት ባልተሰራበት ዓመት በግብር ከፋዮች ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ማድረግ አለበት።

፫/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የንግድ ሥራውን በሚያከናውንበት የግብር ዓመት የነበረው ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ ከ፪ ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን) ብር በላይ የሆነ እንደሆነ፣ ከ፪ ሚሊዮን (ከሁለት ሚሊዮን ብር) በላይ ላለው ገቢ ግብር የሚከፍለው ደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮችን ግብር ማስከፈያ ሰንጠረዥ ከፍተኛ በፍጥጥን ግብር ማስከፈያ ሰንጠረዥ በፍተኛ መጣኔን መሰረት በማድረግ ይሆናል።"

4/ The determination of the annual turnover of a taxpayer for a tax year includes both taxable and exempt income of a taxpayer.

5/ A reference in these Regulations to a "Category "A" taxpayer includes a Category "B" taxpayer to whom Sub-Article (4) of Article 50 of the Proclamation applies.

54. <u>Gross Sales Income of Category "B' Taxpayers</u>

1/ Gross sales income of category "B" taxpayers shall be determined based on the market study of the Tax Authority conducted every three years.

2/ The Tax Authority shall make inflation adjustment on the gross sales income of taxpayers based on the inflation index issued by the Ethiopian Statistics Service appropriate to the business activity in a year in which market study is not conducted.

3/ Where, in a tax year for which a taxpayer has been categorised as a Category "B" taxpayer, the taxpayer's annual gross income exceeds Birr 2,000,000 (two million), tax on the income exceeding Birr 2,000,000 (two million) shall be computed at the highest rate of the tax schedule applicable to Category "B" taxpayers."

CamScanner

፲፪) ከደንቡ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍል ሰባት ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ ክፍል ስምንት፣ ዘጠኝ እና አስር ተጨምረዋል፦

"ንዑስ ክፍል ስምንት

የንግድ ስራ ገቢ ግብር የሚከፈልበት

ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ

፶፭. የንግድ ስራ ገቢ ግብር አከፋፈል

፩/ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ በአዋጁ በተደነገገው መሰረት እንደሁኔታው በሰንጠረዥ "ሐ" በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው መጣኔ ወይም በሰንጠረዥ "መ" በሌሎች ገቢዎች ላይ የተጣለው ፲፭% ግብር ይከፈልበታል።

፪/ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር እንዲከፈልበት የሚደረገው በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተደነገጉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል።

፶፮. የዲጂታል ይዘት ፈጣሪ ግዴታዎች

የንግድ ስራ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት የዲጂታል ይዘት ፈጣሪ ከገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ምንጮች ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ያገኘውን ሁሉንም የገቢ መጠን (በጥሬ ገንዘብም ሆነ በዓይነት ያገኘውን) በሚመለከት፣ ትክክለኛና የተሟላ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን፤ እንዲህ ያሉት መዝገቦች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፦

ሀ) ከማስታወቂያዎች፣ ስፖንሰርሺፖች፣ የደንበኝነት ምዝገባዎች እና ሌሎች ምንጮች የተገኘ ገቢን የሚያሳዩ ከዲጂታል አገልግሎት መድረኮች የተገኙ መግለጫዎች፤

ለ) በዲጂታል መልኩ ከሚደረጉ ሥጦታዎች፤

ሐ) ከስፖንሰሮች እና ከማስታወቂያ አቅራቢዎች ጋር የተደረጉ ስምምነቶች፤

12) The following new sub section eight, nine and ten are added after sub section seven of section five of the Regulation:

"Sub- Section Eight

Income from Digital Content Creation Subject to Business Income Tax

55. Payment of Business Income Tax

1/ Income derived from digital content creation shall be subject to tax, in accordance with the provisions of the Proclamation, at the rates applicable to business income under Schedule 'C' or at the 15% tax rate applicable to other income under Schedule 'D', as the case may be.

2/ Income from digital content creation shall be subject to Schedule "C" business income tax based on the conditions provided under Article 22 Sub-Article (1) of the Proclamation.

56. Obligations of Digital Content Creator

Digital content creator who is liable to pay business income tax shall maintain proper and accurate books of records on income it has received (cash or in kind) from domestic or foreign sources for digital content creation which includes the following:

a) Statements obtained from digital service platforms indicating income derived from advertisements, sponsorships, subscriptions, and other sources;

b) Income derived from gifts made in digital form;

c) agreements concluded with sponsors and advertisers for advertisements;

CamScanner

መ) ክፍያዎችን መቀበልን የሚያሳዩ የባንክ መግለጫዎች፤

ሠ) በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ምትክ የተገኙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና ግምታዊ የገበያ ዋጋቸው፤ እና

ረ) በታክሱ ባለስልጣን ሊጠየቁ የሚችሉ ሌሎች ማናቸውም ሰነዶች።

"ንዑስ ክፍል ዘጠኝ

አማራጭ አነስተኛ ግብር

፶፯. የአማራጭ አነስተኛ ግብር መሰረት

፩/ ትርፍም ሆነ ኪሳራ እንዳልነበራቸው የሚገልጹትን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ እንደሌላቸው ወይም ኪሳራ እንዳጋጠማቸው በመግለጽ የገቢ ማስታወቂያ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ለሚከፍሉት አመታዊ አማራጭ አነስተኛ ግብር መሰረት የሚሆነው ጠቅላላ ገቢ በግብር ዓመቱ ውስጥ ያከናወኑት የእቃ እና የአገልግሎት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ይሆናል።

፪/ በግብር ዓመቱ ምንም አይነት ስራ አልሰራንም በሚል የገቢ ማስታወቂያ የሚያቀርብ ግብር ከፋይ ለሚከፍለው አመታዊ አማራጭ አነስተኛ ግብር መሰረት የሚሆነው ጠቅላላ ገቢ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ድንጋጌዎች እና የታክሱ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በማድረግ በጥናት ላይ ተመስርቶ በግምት ይወሰናል።

d) bank statement showing cash receipts;

e) goods or services received in lieu of cash; and their estimated market value; and

f) Any other documents required by the Tax Authority.

"Sub Section Nine

Minimum Alternative Tax

57. Base for Minimum Alternative Tax

1/ For taxpayers who declare, for the tax year, no taxable income or a loss, including where they declare that they have incurred neither a profit nor a loss, the gross income to be used as the basis for the annual minimum alternative tax shall be the total turnover derived from the sale of goods and services during the tax year.

2/ For a taxpayer who declares that no business activity was conducted during the tax year, the gross income to be used as the basis for the annual minimum alternative tax shall be estimated by the Tax Authority on the basis of a study, in accordance with the Tax Administration Proclamation and the directives to be issued by the Tax Authority.

CamScanner

፫/ ግብር ከፋዩ ሊከፍል የሚገባው አማራጭ አነስተኛ ግብር ከተሰላ በኋላ በግብር ዓመቱ በየሶስት ወሩ የከፈለው የቅድሚያ ግብር፣ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የተያዘበት ግብር እንዲሁም ወደአገር ባስገባቸው እቃዎች ላይ የከፈለው የቅድሚያ ግብር በቅደም ተከተል ከዓመታዊ የግብር መጠን ላይ ተቀናሽ ይደረጋሉ።

3/ After the minimum alternative tax payable by the taxpayer is computed, the advance tax paid quarterly in the tax year, the tax withheld at source from accounts payable, and the advance tax paid on goods imported into the country shall be deducted sequentially from the annual tax amount.

፬/ የአማራጭ አነስተኛ ግብርን ለማስላት የሚወሰደው ግብር የሚከፈልበት ጠቅላላ ገቢ፣ በታክስ ዘመኑ ኪሳራ ካጋጠማቸው የንግድ ሥራዎች የተገኘውን ገቢ ተቀናሽ ወይም ማካካሻ እንዲደረግባቸው ሳይደረግ፣ ከሁሉም የታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች የሚገኘውን ጠቅላላ ገቢ በመደመር ይወሰናል።

4/ For the purposes of calculating the Minimum Alternative Tax liability, the taxable turnover shall be determined by aggregating the total gross turnover derived from all business activities of the taxpayer, without any deduction, exclusion, or offset in respect of gross revenues from business activities that incurred loss during the tax period.

፶፰. <u>አማራጭ አነስተኛ ግብርን ስለማቀናነስ</u>

58. <u>Credit on Minimum Alternative Tax</u>

፩/ ግብር ከፋዩ በአንድ የግብር አመት ከሁሉም የንግድ ስራ የገቢ ምንጮች ባገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ የከፈለው ፪.፭% (ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) አማራጭ አነስተኛ ግብር ሊከፍል ከሚገባው ግብር በላይ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለው ግብር በሚቀጥሉት አምስት አመታት ከሚከፈል ግብር ላይ ተቀናሽ ሊደረግ ይችላል።

1/ Where it is established that the 2.5% (two point five percent) minimum alternative tax paid by a taxpayer on the gross income derived from all business sources in a tax year exceeds the tax actually payable, the amount paid in excess may be carried forward and credited against tax payable in the subsequent five tax years.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፦

2/ The tax credit under Sub Article (1) shall only be granted on the following conditions:

ሀ) ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ የያዘ ከሆነ፤

a) if the taxpayer maintains books of account;

ለ) አማራጭ አነስተኛ ግብር በተከፈለበት የግብር ዓመት ግብር ከፋዩ ሊከፍል የሚገባው ግብር ከአመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከ፪.፭ በመቶ (ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) በታች ሊሆን እንደሚገባ በታክስ ባለስልጣኑ ሲረጋገጥ፤ እና

ሐ) ተቀናሽ በሚደረግበት የግብር ዓመት ግብር ከፋዩ የከፈለው ግብር ከ፪.፭ በመቶ (ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) በላይ ሲሆን እና አማራጭ አነስተኛው ግብር እንደተጠበቀ ሆኖ ለተቀናሽ የሚውል ተከፋይ ግብር ያለ እንደሆነ፤

፫/ አማራጭ አነስተኛ ግብር ያለፉትን አመታት ኪሳራ ወደፊት በማሸጋገር ላይ የሚገኝ ግብር ከፋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል። ስለሆነም ግብር ከፋዩ ካለፉት የግብር አመታት የተሸጋገረ ኪሳራ ያለው እንደሆነ ኪሳራው ሊካካስ የሚችለው በግብር ዓመቱ ሊከፈል ከሚገባው አማራጭ አነስተኛው ግብር በላይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው በሚሆንበት ጊዜ ይሆናል።

፶፱. <u>ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ ስለመሆን</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፭) ከተደነገገው በተጨማሪ መደበኛውን የንግድ ትርፍ ግብር የሚከፍሉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአቅርቦታቸው ታሪፍ በመንግስት የሚወሰን በኤሌክትሪክ እና በውሃ አቅርቦት እንዲሁም በከተማ አውቶቡስ እና በባቡር ትራንስፖርት ስራ ላይ የተሰማሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ ተደርገዋል።

b) if the Tax Authority verifies that the tax liability of the taxpayer in the tax year in which the Minimum Alternative tax paid is lower than 2.5% (two-point five percent) of its gross income; and

c) if the tax liability of the taxpayer in the tax year in which credit can be granted is more than 2.5% (two-point five percent) and the taxpayer has tax payable in excess of the Minimum Alternative Tax Payable in that fiscal year;

3/ The Minimum Alternative Tax shall be applicable to a taxpayer who is currently carrying forward losses from previous years. Accordingly, where a taxpayer has a loss carried forward from previous tax years, such loss may only be deductible if the taxpayer has taxable income in excess of the amount required to satisfy the Minimum Alternative Tax for the current tax year.

59. <u>Exemption from Minimum Alternative Tax</u>

1/ In addition to the provisions of Article 23 Sub Article (5) of the Proclamation and subject to their liability to pay the regular business profit tax, public enterprises engaged in the supply of electricity and water, as well as in urban bus and rail transport services, whose supply tariffs are determined by the Government, are hereby exempted from the minimum alternative tax.

CamScanner

፪/ አማራጭ አነስተኛ ግብር ተፈጻሚ የሚሆነው በአዋጁ ሰንጠረዥ 'ሐ' መሠረት ግብር በሚከፈልባቸው ገቢዎች ላይ ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም ይህ ግብር በሌሎች ሰንጠረዦች መሰረት ግብር ከሚከፈልባቸው ገቢዎች ወይም በሕግ ከግብር ነፃ በተደረጉ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

2/ Minimum Alternative Tax shall be applicable exclusively to income taxable under Schedule 'C' of the Proclamation; provided, however, that such tax shall not apply to income taxable under other Schedules or to income specifically exempted from tax under the law.

፫/ ለአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፮) አፈጻጸም በኪሳራ ላይ ያለ ድርጅት ወይም ዕዳ ማሸጋሸግ ላይ ያለ ድርጅት የሚባሉት በኢትዮጵያ የንግድ ህግ በተደነገገው መሰረት እንደሁኔታው በኪሳራ ላይ ያሉ ስለመሆኑ ወይም ለጥንቃቄ እዳን መልሶ ስለማዋቀር ወይም መልሶ ስለማደራጀት በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ድርጅቶች ናቸው።

3/ For the purposes of the implementation of Article 23 Sub Article (6) of the Proclamation, an entity under liquidation and a corporate body under debt restructuring shall refer to taxpayers on which court decisions are made in relation to bankruptcy, preventive restructuring or debt reorganization in accordance with the Commercial Code of Ethiopia.

፬/ በጦርነት፣ የእርስ በርስ ግጭት፣ በተፈጥሮ አደጋ ወይም ድንገተኛ አደጋ ምክንያት በአንድ የግብር አመት ውስጥ ከስድስት ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ያላከናወነ ግብር ከፋይ ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ ነው።

4/ Taxpayers who have not conducted business activities for more than six months within a tax year due to war, civil conflict, natural disaster, or supervening calamity shall be exempted from the minimum alternative tax.

፷. <u>በኮሚሽን ገቢ ላይ የሚከፈል አማራጭ አነስተኛ ግብር</u>

60. <u>Minimum Alternative Tax Payable on Income from Commission</u>

፩/ የንግድ ወኪሎች እቃዎችን እና አገልግሎቶችን ከአስመጪ ወይም ከአምራች ወይም ከሌላ አገልግሎት ሰጪ በውክልና ተረክበው በወካያቸው ስም የሚሸጡ እና የሸጡበትን ዋጋ ለወካያቸው የሚያስረክቡ ከሆነ አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚከፍሉት በሚያገኙት የኮሚሽን ክፍያ ላይ ነው።

1/ Commercial agents that are engaged in the sale of goods or services in the name of the importer, producer or other service provider and that transfer the selling price to their principal shall pay Minimum Alternative Tax on their commission income.

CamScanner

፪/ የጅምላ ሻጭ ፈቃድ ያላቸው ግብር ከፋዮች ከአምራቹ፤ ከአስመጪው ወይም ከሌላ ጅምላ ሻጭ ጋር ባደረጉት ውል መሰረት ለችርቻሪዎች ወይም ለሌሎች ጅምላ ሻጮች የሚሸጡበት ዋጋ እና ከሽያጩ የሚኖራቸው ድርሻ በመቶኛ የተወሰነ ከሆነ አማራጭ አነስተኛ ግብሩ የሚሰላው በሚከፈላቸው መቶኛ ላይ ይሆናል።

2/ Taxpayers who have wholesale trade license that are engaged in the distribution of goods to other wholesalers or retailers based on the contract concluded with the importer or producer and whose margin is determined by such contract shall pay the Minimum Alternative Tax on the margin paid to them.

፫/ አምራቹ ወይም አስመጪው እና የጅምላ ሻጩ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን በውል የወሰኑ ከሆነ እና ጅምላ ሻጩ የሚያስከፍለው መቶኛ መጠን በተመሳሳይ በውሉ ከተወሰነ፣ የታክሱ ባለስልጣን የአስመጪውን ወይም የአምራቹን ሂሳብ በሚመረምርበት ጊዜ የዚህ አይነት ውሎችን በአንድነት ማየት አለበት።

3/ Where a manufacturer or importer and a wholesaler have contractually determined the retail selling price, and the wholesaler's commission percentage is likewise fixed by the contract, the Tax Authority shall examine such contracts collectively when auditing the accounts of the importer or the manufacturer.

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም በአምራች ወይም በአስመጪ እና በጅምላ ሻጩ መካከል ዋጋን የሚወስን ውል ቢኖርም፤ አማራጭ አነስተኛ ግብር በውሉ ላይ በተቀመጠው የዋጋ መቶኛ መነሻነት ሊሰላ የሚችለው፣ አከፋፋዩ ከአምራቹ ወይም ከአስመጪው የገዛበትን ዋጋ የሚያሳይ ደረሰኝ፣ ለችርቻሪዎች ወይም ለሌሎች ወገኖች ሽያጭ የፈጸመበትን ሕጋዊ ደረሰኝ እና ሌሎች ለጉዳዩ አስፈላጊ የሆኑ የሂሳብ ሰነዶችን ለታክስ ባለሥልጣኑ አቅርቦ ሲመረመሩ ብቻ ይሆናል።

4/ For the purposes of Sub-Article (3) of this Article, notwithstanding the existence of a price determining contract between a manufacturer or importer and a wholesaler, the minimum alternative tax shall be calculated based on the price percentage set in the contract only if the wholesaler presents to the Tax Authority for audit the invoices showing the purchase price from the manufacturer or importer, invoices for sales made to retailers or other parties, and other accounting documents related to the case.

CamScanner

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት አከፋፋዩ ምርት ወይም አገልግሎቱን ለገበያ ያቀረበው በአምራቹ ወይም በአስመጪው በተወሰነው የዋጋ ልክ ስለመሆኑ መረጋገጥ አለበት። ሆኖም የቀረቡት ሰነዶች ይህንን ማረጋገጥ የማይችሉ ሆነው ከተገኙ ወይም ከስምምነቱ ውጪ ግብይት መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣ የታክስ ባለሥልጣኑ የግብር ከፋዩን ዓመታዊ ሽያጭ መሰረት በማድረግ አማራጭ አነስተኛ ግብሩን ተፈፃሚ ያደርጋል።

5/ In accordance with Sub-Article (4) of this Article, it must be verified that the wholesaler has sold the goods or services at the price levels determined by the manufacturer or importer. However, if the submitted documents fail to verify this, or if it is established that transactions were conducted outside the terms of the agreement, the Authority shall apply the minimum alternative tax based on the taxpayer's annual sales.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት በአምራቹ ወይም በአስመጪው በተወሰነው ዋጋ መሠረት ግብይት መፈጸሙን በማስታወቅ አማራጭ አነስተኛ ግብር የከፈለ ግብር ከፋይ ሂሳቡ በሚመረመርበት ወቅት ከስምምነቱ ውጭ ግብይት መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣ ቀደም ሲል በታክስ ማስታወቂያው ወቅት የከፈለው አማራጭ አነስተኛ ግብር በታክስ አስተዳደር አዋጁ በተወሰነው ጊዜ በታክስ ባለስልጣኑ እንደገና ተሰልቶ፣ በተሰላው እና ቀደም ሲል በተከፈለው አማራጭ አነስተኛ ግብር መካከል ያለው ልዩነት በግብር ከፋዩ እንዲከፈል ይደረጋል።

6/ Where a taxpayer who paid minimum alternative tax by declaring that transactions were conducted in accordance with the price determined by the manufacturer or importer pursuant to Sub-Article (5) of this Article is found, during an audit of their accounts, to have transacted outside of the agreement, the minimum alternative tax previously paid during the tax declaration period shall be recalculated by the Tax Authority within the period specified under the Tax Administration Proclamation, and the difference between the recalculated amount and the previously paid minimum alternative tax shall be paid by the taxpayer.

CamScanner

ንዑስ ክፍል አስር

ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር የግብር አከፋፈል

፷፩. ጠቅላላ

፩/ ለደንቡ የዚህ ንዑስ ክፍል ዓላማ፤

ሀ) "የሚከፋፈል ገቢ" ማለት ሁሉም የሚፈቀዱ የንግድ ሥራ ወጪዎችን ማህበሩ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ካገኘው ከጠቅላላ ገቢ ላይ በመቀነስ የሚያገኘው አጠቃላይ የተጣራ ትርፍ ነው።

ለ) ለዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል "ሀ" ዓላማ እንደ ደመወዝ፣ ድሮዊንግ (የማህበሩን ገንዘብ ለግል ጥቅም መውሰድ)፣ የተረጋገጡ ክፍያዎች ወይም የትርፍ ድርሻዎችን ጨምሮ ሌሎች ለአባላት የሚደረጉ ማናቸውም ክፍያዎች እንደ ተቀናሽ የንግድ ወጪዎች አይቆጠሩም፣ ሆኖም የገቢ ክፍፍል እንደሆኑ ይቆጠራሉ።

፪/ የዚህ የደንቡ ክፍል ድንጋጌዎች የህብረት ስራ ማህበራትን በሚመለከትም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

፷፪. የአባላት ግብር አከፋፈል

፩/ እያንዳንዱ የማህበሩ አባል በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ከማህበሩ በሚከፋፈል ገቢ ላይ ባላቸው የድርሻ መጠን መሰረት በየግላቸው ለገቢ ግብር ተጠያቂ የሚሆኑ ሲሆን፣ ማህበሩ ለአባላቱ በሚያከፋፍለው ገቢ ላይ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብሩን ቀንሶ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።

Sub Section Ten

Payment of Tax by Limited Liability Partnerships

61. General

1/ For purposes of this sub-section of the Regulation;

a) **"Income for distribution"** means the total net profit of Limited Liability Partnership after all allowable deductions are made from the annual gross income;

b) For the purpose of paragraph (a) this Article, wages; drawings (drawing the income of Limited Liability Partnership for personal use); guaranteed payments or dividends or other payments to partners shall not be considered as deductibles allowed but considered as distributions of income.

2/ The provisions of this Section of the Regulation shall also be applicable to Cooperative Societies.

62. Payment of Tax by Partners

1/ Each member of the partnership shall be individually liable for income tax on the income distributed by the partnership in a tax year in proportion to its respective shares; the partnership shall withhold the tax from the income distributed to its members in accordance with Schedule 'C' and remit the same to the Tax Authority.

CamScanner

፪/ አንድ አባል ከሚከፋፈል ገቢ ላይ ያለው ድርሻ የሚወሰነው በማህበሩ የሽርክና ስምምነት መሰረት ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ስምምነት ድርሻቸውን በግልጽ የማያሳይ በሚሆንበት ጊዜ፣ ገቢው በአባላቱ መካከል እኩል ይከፋፈላል።

2/ The share of each partner from the income for distribution shall be as determined by the Partnership Agreement. Where the Partnership Agreement does not specify the share of each partner the income for distribution shall be distributed equally to all partners.

፫/ ለግብር ዓመቱ የአባሉን አጠቃላይ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን አንድ አባል ከማህበሩ የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ስሌት ውስጥ ይካተታል።

3/ For the purpose of determining the member's total taxable income for the tax year, the gross income derived by a member from the partnership shall be included in the calculation.

፬/ ማህበሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፫ መሠረት ቀንሶ የያዘው ግብር ለአባሉ በተከፋፈለው ገቢ ላይ የመጨረሻ ነው።

4/ Tax withheld by the Partnership under Article 63 of this Regulation shall be a final tax on the income distributed to the member.

፷፫. <u>ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ</u>

63. <u>Duty to Withhold Tax</u>

፩/ ደመወዝን ጨምሮ አንድ ማህበር ለአባላቱ በሚያደርገው ማንኛውም የገንዘብ ክፍፍል ላይ የገቢ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት።

1/ A Partnership has the obligation to withhold tax from any distribution of income, including salary, to its partners.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው የክፍፍል ገንዘቡ በተከፈለበት ወይም በአባሉ ሂሳብ ገቢ በተደረገበት ጊዜ ውስጥ ቀድሞ በተፈጸመው ጊዜ ነው።

2/ The obligation to withhold tax under sub article 1 of this Article shall be applicable at the time of distribution of income or when the distribution is recorded in the name of the partner; whichever is earlier.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ የሽርክና ማህበር ከግብር ዓመቱ ማብቂያ ጀምሮ በሚቆጠር የ፫ (ሦስት) ወራት ጊዜ ውስጥ ገቢውን ካላከፋፈለ፣ ገቢው እንደተከፋፈለ ተቆጥሮ ግብር ይከፈልበታል።

3/ Subject to Sub Articles (1) and (2) of this Article, where a Partnership has not distributed the income within 3 (Three) months from the end of the tax year, the tax shall be paid as though the distribution had been made.

CamScanner

፬/ በማህበሩ ተቀንሶ የሚያዘው የግብር መጠን የሚሰላው ከሚከፋፈለው ጠቅላላ የገቢ መጠን ላይ ምንም ቅናሽ ሳይደረግበት ሲሆን፣ በአዋጁ ሰንጠረዥ "ሐ" ለግለሰብ ግብር ከፋይ በተቀመጠው የታክስ መጣኔ መሰረት ግብሩ ተቀንሶ ገቢ መደረግ አለበት።

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም፣ የማህበሩ አባል ድርጅት በሆነ ጊዜ ለዚያ አባል ከሚከፋፈለው ገቢ ላይ ተቀንሶ የሚያዘው ግብር የሚሰላው በአዋጁ ሰንጠረዥ "ሐ" ለድርጅቶች በተቀመጠው የግብር መጣኔ መሠረት ይሆናል።

4/ The amount of tax to be withheld by a Partnership shall be calculated on the gross amount of the distributable income without any deductions, and such tax shall be withheld and remitted in accordance with the tax rates applicable to individual taxpayers under Schedule 'C' of the Proclamation.

5/ Notwithstanding Sub-Article (4) of this Article, where a member of the Partnership is a body, the tax to be withheld from the income distributed to that member shall be computed at the rate applicable to bodies under Schedule "C" of the Proclamation.

፷፬. <u>የተቀነሰ ግብርን ስለመክፈል</u>

64. <u>Payment of tax Withheld</u>

፩/ ማህበሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፫ መሰረት ቀንሶ ያስቀረውን የግብር መጠን ግብሩ ከተቀነሰበት ወር ማብቂያ ጀምሮ በሚቆጠር የሰላሳ (፴) ቀናት ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት።

1/ The Partnership shall remit the amount of tax withheld in accordance with Article 63 of this Regulation to the Tax Authority within Thirty (30) days from the end of the month in which the tax was withheld.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ገንዘብ ገቢ ከሚደረግበት ሰነድ ጋር የታክስ ባለስልጣኑ በሚወሰነው ቅጽ መሰረት አጠቃላይ የተከፋፈለው መጠን፣ የአባላቱ ስም እና ከእያንዳንዱ አባል ላይ የተቀነሰው የግብር መጠን ዝርዝር መቅረብ አለበት።

2/ A Partnership shall submit, with the payment under sub-article (1) and in the form prescribed by the Tax Authority, a statement showing the total income distributed, the names of the partners and the tax withheld from each partner."

፫/ የሽርክና ማህበሩም ሆነ የማህበሩ አባላት በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የየራሳቸው የሆነ የቅድሚያ ግብር የመክፈል ግዴታ የለባቸውም።

3/ Neither the Partnership nor the members of the Partnership shall be obligated to pay quarterly installment tax under the Proclamation and this Regulation.

CamScanner

፷፭. <u>ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫን ስለማቅረብ</u>

፩/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር በአዋጁ መሰረት ሂሳብ መግለጫ ለማቅረብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ በታክስ ባለስልጣኑ በተወሰነው ቅጽ መሰረት ሲሆን፤ ቢያንስ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፤

ሀ) የማህበሩ አጠቃላይ ገቢ፣ ወጪዎች እና በግብር ዓመቱ የተከፋፈለ ገቢ፣

ለ) የሁሉም አባላት ስም እና ከሚከፋፈለው ወይም ከተከፋፈለው ገቢ ያላቸው የድርሻ መጠን፣

ሐ) በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉት አጠቃላይ ክፍፍሎች እና አጠቃላይ የተቀነሰው ግብር፣ እና

መ) የታክስ ባለስልጣኑ ሊጠይቀው የሚችል ሌላ ማንኛውም መረጃ።

፷፮. <u>ማህበሩ ግብሩን ቀንሶ ባለመያዙ የሚኖርበት ተጠያቂነት</u>

በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሰረት ቀንሶ መያዝ ያለበትን ግብር ቀንሶ ለመያዝ ያልቻለ ወይም ቀንሶ የያዘውን ግብር ለታክስ ባለስልጣኑ ያልከፈለ ማህበር፣ በአዋጁ አንቀጽ ፺፱፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት መክፈል የሚኖርበትን ግብር በተመለከተ ኃላፊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ግብርን ባለማስታወቅ እና ባለመክፈል የተጣሉ ቅጣቶችን እና ወለድ ይከፍላል።

65. <u>Submission of Annual Financial Report</u>

1/ A Limited Liability Partnership shall submit its annual financial report to the Tax Authority within the time limit prescribed under the Proclamation for the submission of financial statements.

2/ The financial report to be submitted in accordance with Sub Article (1) of this Article shall be prepared on the prescribed form determined by the Tax Authority and shall contain at least the following:

a) The gross income of the Partnership, expenses and the income distributed in the tax year,

b) The names of all partners and their share from the distributed income or the income to be distributed,

c) The total distribution made in a tax year and the total amount of tax withheld, and

d) Any other information required by the Tax Authority.

66. <u>Liability of the Partnership for failure to withhold the Tax</u>

A Partnership that fails to withhold tax required to be withheld under the Proclamation and this Regulation, or fails to remit tax withheld shall be liable to pay penalty for failure to file the return and for not paying taxes as well as the interest thereon in accordance with the Tax Administration Proclamation, without prejudice to its liability regarding the tax payable in accordance with Article 102 Sub Article (3) of the Proclamation.

CamScanner

፷፯. <u>ማህበሩ ተቀንሶ ከሚያዝ ግብር ነጻ ስለመሆኑ</u>

፩/ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚቀበለው ክፍያ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፺፯ መሰረት ተቀንሶ ከሚያዝ ግብር ነጻ ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማህበሩ በሚፈጽማቸው የዕቃ እና አገልግሎት ግዥዎች ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፺፯ የተደነገገውን ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት አለበት።

፫/ በደንቡ ክፍል ስድስት ከአንቀጽ ፶ እስከ ፶፫ ወይም በተሸጋገው ከአንቀጽ ፷፰ እስከ ፸፩ ያሉት ድንጋጌዎች **"ንዑስ ክፍል አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌዎች"** የሚል አርዕስት ባለው አዲስ ንዑስ ክፍል ስር ተካተዋል።

፲፫) የደንቡ አንቀጽ ፶፩ ወይም በተሸጋገው አንቀጽ ፷፱ ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፷፱ ተተክቷል፦

"፷፱. <u>በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወደ ውጭ የሚልከው ትርፍ</u>

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ወደ ውጭ በሚልከው ትርፍ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፷፭ መሠረት ግብር የሚጣለው የድርጅቱን የግብር ዓመት መሠረት በማድረግ ወደ ውጭ በሚላከው በጠቅላላው የትርፍ መጠን ላይ ይሆናል።

፪/ በቋሚነት የሚሰራው ድርጅት የግብር ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት ፲፪ (አሥራ ሁለት) ወራት ጊዜ ውስጥ ትርፉን ወደውጭ አገር ባይልክም፣ ትርፉ እንደተላከ ተቆጥሮ በአዋጁ አንቀጽ ፷፭ መሰረት ግብሩ ተፈጻሚ ይሆናል።

67. <u>Exemption of Partnership from Withholding</u>

1/ A Limited Liability Partnership shall be exempt from a withholding tax on payments it received for services rendered in accordance with Article 97 of the Proclamation.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Partnership shall have the obligation to withhold tax on payments made for the purchase of goods and services in accordance with Article 97 of the Proclamation.

3/ Articles 50 to 53 or the renumbered Articles 68 to 71 of Section Six of the Regulation are hereby incorporated under a new sub section under the title "**Sub-Section One – General Provisions**".

13) Article 51 of the Regulation or Article 69 as renumbered is repealed and replaced by the following new Article 69:

"69. <u>Profit Repatriated by a Permanent Establishment</u>

1/ A non-resident body carrying on business in Ethiopia through a permanent establishment shall be subject to tax, pursuant to Article 65 of the Proclamation, on the aggregate amount of profit repatriated based on the tax year of the body.

2/ Profit that has not been repatriated by the permanent establishment within 12 (Twelve) months following the end of the tax year shall be deemed to have been repatriated, and the tax shall apply in accordance with Article 65 of the Proclamation.

CamScanner

፫/ በቋሚነት የሚሰራው ድርጅት ትርፉን ወደ ውጭ አገር ሳያስተላልፍ ሥራውን በቋሚነት የሚያቋርጥ ወይም የሚዘጋ ከሆነ፣ በሂሳብ መዝገቡ ላይ የሚታየው ማንኛውም ወደውጭ አገር ያልተላከ የተጣራ ትርፍ እንደተላከ ተቆጥሮ በመጨረሻው የሂሳብ ማጠቃለያ ወቅት ግብሩን እንዲከፍል ይገደዳል።

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ግብር የተከፈለበት ትርፍ በትክክል ወደ ውጭ አገር በሚላክበት ወቅት፣ በዚህ ገቢ ላይ ቀደም ሲል ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ሲቀርብ፣ ወደ ውጭ አገር በተላከው የገንዘብ መጠን ላይ በድጋሚ የግብር ክፍያ እንዲፈጸም አይጠየቅም።

፭/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በቋሚነት የሚሰራው ድርጅት ትርፉን ወደ ውጭ አገር ሲልክ የባንክ የገንዘብ ማስተላለፊያ ሰነዱን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።"

፲፬) ከደንቡ ክፍል ስድስት ንዑስ ክፍል አንድ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ ክፍል ሁለት ተጨምሯል፦

"ንዑስ ክፍል ሁለት

በሰንጠረዥ "መ" መሰረት ግብር

ስለሚከፈልበት ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ

የሚገኝ ገቢ

፸፪. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አስፈላጊ ስለመሆኑ

በሰንጠረዥ "መ" መሰረት ግብር የሚከፍል ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ገቢ የሚያገኝ ሰው በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት በመመዝገብ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል።

3/ Where a permanent establishment permanently ceases or liquidates its business without repatriating its profit, any undistributed net profit recorded in its books of account shall be deemed to have been repatriated, and the tax thereon shall become due and payable at the time of final accounting settlement.

4/ Where profit upon which tax has been paid pursuant to this Article is subsequently repatriated, no further tax shall be assessed on the repatriated amount, provided that proof of prior tax payment on such income is submitted to the Authority.

5/ For the purposes of this Article, a permanent establishment repatriating profit abroad shall submit the corresponding bank transfer documentation to the Authority."

14) The following new Sub-Section Two is added after Sub-Section One of Section Six of the Regulation:

"Sub-Section Two

Income from Digital Content Creation subject to Tax under Schedule "D"

72. The Requirement to have Tax payer Identification Number

A taxpayer receiving income from digital content creation and subject to tax under Schedule "D" shall register and have taxpayer identification number in accordance with the Tax Administration Proclamation.

፹፫. የግብር የማስከፈያ መጣኔ

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፭ የተዘረዘሩትን የማያሟላ ከዲጂታል ፈጠራ ገቢ የሚያገኝ ሰው ሌሎች ገቢዎች በሚለው በአዋጁ የሰንጠረዥ "መ" ግብር ማስከፈያ መጣኔ መሰረት ፲፭ በመቶ (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፍላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ገቢ በሚያገኝ የኢትዮጵያ ነዋሪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፫/ ለዚህ ንዑስ ክፍል አፈፃፀም የዲጂታል አገልግሎት መድረክ አካውንት የተከፈተው ከኢትዮጵያ ውጪ መሆኑ ወይም ክፍያ የሚፈጸመው ከኢትዮጵያ ውጪ መሆኑ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነን የዲጂታል ይዘት ፈጣሪ የግብር ተጠያቂነት የሚያስቀር አይሆንም።

73. Tax Rate

1/ A taxpayer who receives income from digital content creation and who does not fulfil the conditions laid down in Article 55 of the Regulations shall pay 15% (Fifteen percent) tax under "Other Income" provided in Schedule "D" of the Proclamation.

2/ The provisions of Sub Article (1) of this Article applies to on residents of Ethiopia who receive income from digital content creation.

3/ For purposes of this Sub-Section, the fact that the account in the platform is opened outside of Ethiopia or income from digital services is received outside of Ethiopia does not relieve the resident digital content creator from paying taxes on the income it has received from digital content creation.

፹፬. ግብር የሚከፈልበት ጠቅላላ ገቢ

፩/ በሰንጠረዥ "መ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ገቢ የሚያገኝ ሰው ግብር እንዲከፍል የሚገደደው ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር ፶ሺህ (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ ከሆነ ነው፤ ስለሆነም ግብር ከፋዩ በአንድ ዓመት ውስጥ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ያገኘው ገቢ ከብር ፶ሺህ (ሃምሳ ሺህ) የማይበልጥ ከሆነ የከፈለው ግብር ለወደፊት ከሚከፍለው ግብር ጋር እንዲካካስ ወይም ተመላሽ እንዲሆን ይደረጋል።

፪/ ሚኒስቴሩ የገንዘብን የመግዛት አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በመመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

74. Taxable Gross Income

1/ A person that has income from digital content creation that falls under Schedule "D" is liable to pay tax if the annual gross income is over Birr 50,000 (Fifty Thousand Birr); Where, however, the income derived by a taxpayer from digital content creation within a single year does not exceed Birr 50,000 (Fifty Thousand Birr), the tax paid shall be credited against future tax liabilities or shall be refunded.

2/ The Ministry may, by Directive, adjust the monetary amount specified in Sub-Article (1) of this Article, taking into account the purchasing power of money.

CamScanner

፹፭. <u>ግብር የሚከፈልበት ጊዜ እና አከፋፈሉ</u>

፩/ በሰንጠረዥ "መ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ገቢ የሚያገኝ ሰው ገቢውን በማስታወቅ በሚያገኘው ገቢ ላይ በየሩብ ዓመቱ ግብር መክፈል አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የሩብ ዓመቱ የግብር ክፍያ ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር በእያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት ውስጥ ያለው ሩብ ዓመት ሲሆን፤ ታክሱ እያንዳንዱ ሩብ አመት በተጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት።

፫/ ለእያንዳንዱ ሩብ ዓመት የሚከፈለው የግብር መጠን የሚሰላው በዚያ ሩብ ዓመት ውስጥ የተገኘውን ገቢ መሰረት በማድረግ ይሆናል።

75. <u>Time and Mode of Payment of the Tax</u>

1/ A person who has an income from digital content creation taxable under Schedule "D" shall declare his income and pay the tax every quarter.

2/ The quarter specified under Sub Article (1) of this Article shall be every quarter commencing from 7th July in every tax year and the tax shall be paid within 30 days after the end of each quarter.

3/ The base for the tax payable in every quarter shall be the income received in that quarter.

፹፮. <u>ለዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያ የሚያመቻች የኦንላይን መድረክ ኃላፊነቶች</u>

፩/ ለዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያ የሚያመቻች የኦንላይን መድረክ የክፍያ ጥያቄ የቀረበበትን አድራሻ፤ የሲምካርድ፤ የአይፒ አድራሻ እና ሌሎችንም መረጃዎች መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ የዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎችን ስም ዝርዝር፤ አድራሻ፤ የተከፈላቸውን ገንዘብ መጠን እና ሌሎችንም በታክሱ ባለስልጣን የሚጠየቁ መረጃዎች በየሩብ አመቱ ለታክሱ ባለስልጣን መላክ አለበት።

፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ለዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያ የሚያመቻች መድረክ እንደ ሁኔታው የዲጂታል መድረክን፣ ለማስታወቂያ ክፍያ የሚፈጽምን እና ተመሳሳይ ድርጅቶችን ይጨምራል።

76. <u>Responsibilities of an online platform facilitating payment for digital content creators</u>

1/ Any platform that facilitates payments for digital content creators shall, based on the address from which the payment request originated, SIM card data, IP address, and other relevant information, submit to the Tax Authority on a quarterly basis the list of names and addresses of digital content creators resident in Ethiopia, the amount of money paid to them, and any other information as may be requested by the Tax Authority.

2/ For the purpose of this Article, a platform that facilitates payments for digital content creators shall, as the case may be, include digital platforms, entities making payments for advertisements, and other similar organizations.

CamScanner

፸፯. የታክሱ ባለስልጣን ኃላፊነቶች

የታክሱ ባለስልጣን የዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎችን እንቅስቃሴ መከታተል እና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለባቸውን መለየት እና የዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎችን ገቢ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ከአገር ውስጥ እና ከዓለም አቀፍ የዲጂታል አገልግሎት ሰጪ መድረኮች ጋር የመተባበር ኃላፊነት አለበት።

፲፭) የደንቡ አንቀጽ ፶፬ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፸፰ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፸፰ ተተክቷል፦

"፸፰. ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ

፩/ የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፡-

ሀ) መንግሥት ለገበያ ከሚያቀርባቸው ማናቸውም ቦንዶች እና የግምጃ ቤት ሰነዶች የሚገኝ ወለድ ወይም ትርፍ፤

ለ) በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ ባገኘ የሰነደ-ሙለ ንዋይ ገበያ በተመዘገበ ቦንድ ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ ሰው ቦንዱን ያወጣው አካል የወለድ ክፍያ መክፈል ከጀመረበት ቀን አንስቶ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ከሚያገኘው የወለድ ገቢ ላይ ከሚከፈል የገቢ ግብር ነፃ ነው፤ ሆኖም የሦስት ዓመት የጊዜ ገደቡ ካበቃ በኋላ በሚገኝ የወለድ ገቢ ላይ በሕጉ መሠረት ተገቢው ግብር ተፈጻሚ ይሆናል።

77. Responsibilities of the Tax Authority

The Tax Authority shall be responsible for following up the activities of digital content creators, identifying their tax liabilities and cooperating with local and international digital platforms to obtain information on income received by digital content creators.

15) Article 54 or renumbered Article 78 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 78:

"78. Income Exempt from Tax

1/ The following income is exempt from tax:

a) Interest or profit from bonds and treasury bills made available to the market by the Government;

b) Any person who invests in a bond listed on a securities exchange licensed by the Ethiopian Capital Market Authority shall be exempted from income tax on interest income derived therefrom for Three consecutive years, calculated from the date the issuer commences interest payments; provided, however, that the appropriate tax shall be applicable in accordance with the law on interest income derived after the expiry of the Three-year period.

CamScanner

ሐ) በአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ለአንድ ቀጣሪ የሰጠው አገልግሎት ሲደመር ከአንድ ወር የማይበልጥ ከሆነ ተቀጣሪው የሚከፍለው ግብር የሚታሰበው የመጨረሻው ቅጥር ባገኘው ገቢ ላይ ብቻ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማንኛውም የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪ ሳያቋርጥ ሆነ በተደጋጋሚ ከሰላሳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ በሚያገኘው ገቢ፤

c) Income from employment received by an unskilled employee working for the same employer whether continuously or intermittently for not more than Thirty (30) days within any Twelve (12) month period, however that the tax payable on income from employment received by a casual employee working intermittently for the same employer for more than Thirty (30) days within Twelve months period shall be calculated only on the income received by that employee from the last employment.

መ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ግብር ከፋዮች በውጭ አገር ነዋሪ ከሆኑ ድርጅቶች ለአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚጠቀሙባቸው አውሮፕላኖች የሚያገኙት የጥገና አገልግሎት፣ የሳተላይት መረጃ፣ ኢንሹራንስ፣ ቴክኒካልና ለሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚፈጽሟቸው ክፍያዎች፣ ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች በሚያገኙት የውጭ አገር ብድር ላይ የሚከፍሉት የወለድ እና ከውጪ አገር ለሚከራዩት አውሮፕላን የሚከፍሉት ሮያሊቲ፤

d) Payments made by taxpayers resident in Ethiopia to non-resident organizations in relation to air transport services for aircraft maintenance services, satellite data, insurance, technical and other similar technical and other services; interest paid on foreign loans obtained from non-related persons; and royalties paid for aircraft leased from abroad;

ሠ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ለአባላቱ በሚያከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ላይ ግብር ቀንሶ ማስቀረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአክሲዮን ባለቤት ከሆነባቸው ድርጅቶች የሚያገኘው የትርፍ ድርሻ ገቢ፤

e) Without prejudice to the Collective Investment Fund's obligation to withhold tax on dividends distributed to its members, dividend income derived by the Fund from companies in which it holds shares;

ረ) በነፃ የንግድ ቀጠናዎች ውስጥ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች ወደአገር ያስገቡትን እቃ በቀጠናው ውስጥ ለተሰማሩ ሌሎች ባለሃብቶች እና ለውጭ አገር ገበያ በማቅረብ የሚያገኙት ገቢ፤

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) አፈጻጸም "ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ" ማለት መደበኛ የሙያ ስልጠና ያልወሰደ ልዩ ሙያ በሚጠይቁ ማሽኖችና መሳሪያዎች የማይጠቀም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ከ፴ ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የተቀጠረ ግለሰብ ነው።

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት ከግብር ነጻ የተደረገው አሰሪው ሰራተኛው ሲታመም ለሰራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ በሰራተኞች የጤና መድን እቅድ መሰረት አሰሪው ለሰራተኞች ጥቅም የሚከፍለውን አረቦን ይጨምራል።"

፲፮) የደንቡ አንቀጽ ፶፮ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፹ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፹ ተተክቷል፦

"፹. <u>ወጪ</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፩ መሠረት ግብር የሚከፈልበት የካፒታል ጥቅም በሚሰላበት ጊዜ የሀብቱ ዋጋ በአዋጁ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረግበታል። የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የሚደረገው ንብረቱ በግብር ከፋዩ ባለቤትነት ስር ከዋለ አንድ አመት እና ከዚያ በላይ ከሆነው ብቻ ነው።

f) Income derived by investors operating in Free Trade Zones from the sale of goods imported from abroad to investors within the Free Trade Zone and reexported abroad.

2/ For the purpose of the exception under Paragraph (c) of this Article "**unskilled employee**" means an employee who has not received vocational, training, does not use machinery or equipment requiring special skill and who is engaged by an employer for a period aggregating not more than Thirty (30) days during a calendar year.

3/ The exemption accorded under Article 68 Sub Article (1) of Paragraph (a) of the Proclamation to an amount paid by an employer to cover the cost of medical treatment of an employee shall include premium payments made by an employer on behalf of an employee under employee's medical insurance scheme."

16) Article 56 or renumbered Article 80 is deleted and replaced by the following new Article 80:

"**80. <u>Cost</u>**

1/ For the purposes of Article 61 of the Proclamation, the cost of a taxable asset shall be adjusted for inflation in accordance with Proclamation and Sub-Article (3) of this Article when computing the taxable gain. The inflation adjustment shall only be applied if the asset has been under the ownership of the taxpayer for One year or more.

፪/ አንድ ግብር ከፋይ በባለቤትነት የሚይዘው ሀብት፡-

ሀ) በአዋጁ መሠረት ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለል የገንዘብ መጠን ከሆነ፣ የሀብቱ ዋጋ ሀብቱን በባለቤትነት ለመያዝ በግብር ከፋዩ የተከፈለን ማንኛውንም የገንዘብ መጠን እና ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለለውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል፤ ወይም

ለ) ከግብር ነጻ የሆነ ገቢ ከሆነ፣ የሃብቱ ዋጋ ሀብቱን በባለቤትነት ለመያዝ በግብር ከፋዩ የተከፈለን ማንኛውንም የገንዘብ መጠን እና ከግብር ነጻ የሆነውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል።

2/ If the acquisition of an asset by a taxpayer is the derivation of an amount that is:

a) included in the income of the taxpayer subject to tax under the Proclamation, the cost of the asset is the amount so included plus any amount paid by the taxpayer for the asset; or

b) Exempt income, the cost of the asset is the exempt amount plus any amount paid by the taxpayer for the asset.

፫/ ለአዋጁ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈጻፀም የዋጋ ንረት ማስተካከያ የሚደረገው ሀብቱ የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ በ፴በመቶ (ሠላሳ በመቶ) በሚከተለው ቀመር ተሰልቶ ይሆናል፤

ለ = ሀ x 30%

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-

ሀ - የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ

ለ - የዋጋ ንረት ማስተካከያ"

3/ For the implementation of Article 61 Sub-Article (3) of the Proclamation, the inflation adjustment shall be calculated at 30% (thirty percent) of the acquisition cost of the asset, and shall be expressed by the following formula:

B = A x 30%

For the purpose of this formula:

A - Acquisition cost

B - Inflation adjustment"

፲፯/ የደንቡ አንቀጽ ፶፰ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፹፪ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፹፪ ተተክቷል፡-

17) Article 58 or renumbered Article 82 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 82:

“፹፪. **የሂሳብ መዝገብ አያያዝ**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ (፰) በተደነገገው መሰረት ከአንድ በላይ ከሆነ የስራ መስክ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋይ ወይም ማናቸውም የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለእያንዳንዱ የተለየ የስራ መስክ በተናጠል የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ ሰነዶችን መያዝ አለበት።

፪/ ከአንድ በላይ በሆነ የሥራ መስክ የተሰማራ ግብር ከፋይ ገቢ የሚጣመረው ኪሳራ ያጋጠመውን የሥራ መስክ ሳይጨምር ከእያንዳንዱ የስራ መስክ ያገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚመለከት ብቻ ይሆናል።

፫/ ከአንድ በላይ በሆነ የሥራ መስክ የተሰማራ ግለሰብ ግብር ከፋይ በሰንጠረዥ “ሐ” መሰረት የሚከፍለው ግብር በሚሰላበት ጊዜ ግብር ነጻ የሆነውን መጠን ተጠቃሚ መሆን የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

፬/ ከአንድ በላይ ከሆነ የሥራ መስክ ገቢ የሚያገኝ ግብር ከፋይ ለእያንዳንዱ የሥራ መስክ በተናጠል የትርፍ እና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ መያዝ ያለበት ሲሆን የሀብት እና ዕዳ የሂሳብ መግለጫን አጠቃሎ ለማቅረብ ይችላል።

፭/ ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማመንጨት በጋራ የሚጠቀምባቸው ቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ እና ወጪዎች ለተለዩ የንግድ ስራ መስኮች የሚደለደሉበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የወጪ አያያዝ መመሪያ ይወሰናል።

“ 82. **Maintenance of Books of Account**

1/ **As** provided under Article 86 Sub-Article (8) of the Proclamation Category “A” taxpayer receiving income from more than one sectors or taxpayer that has an obligation to maintain books of account, shall maintain separate books of account and documents for each sector.

2/ Aggregation of income of a taxpayer engaged in more than one sectors shall only be made on the taxable income obtained from each sector, excluding any line of business in which a loss has been incurred.

3/ Where an individual taxpayer is engaged in more than one business sector, the tax-exempt threshold shall be applied only once when calculating the tax payable pursuant to Schedule 'C'.

4/ A taxpayer receiving income from more than one sectors shall maintain separate profit and loss statement and may maintain consolidated statement of asset and liability.

5/ Apportionment of depreciation of fixed assets jointly used in generating the income and expenses incurred for joint activities of the sectors shall be made in accordance with the Directive on deductible expenses to be issued by the Ministry.

CamScanner

፮/ በሰንጠረዥ "ለ" መሰረት የኪራይ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ "ሀ" ግለሰብ ግብር ከፋይ የሒሳብ መዝገብ ካልያዘ ከጠቅላላ የኪራይ ገቢው ላይ ፹ በመቶ (ሰማንያ በመቶ) ታክስ የሚከፈልበት ገቢ እንደሆነ ተቆጥሮ በሰንጠረዥ "ለ" መሰረት ግብር ይከፍላል።

6/ A Category 'A' individual taxpayer deriving rental income under Schedule 'B' who fails to maintain books of account shall be taxed on 80% (Eighty percent) of the gross rental income, which shall be deemed as taxable income and taxed in accordance with Schedule 'B'.

፯/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ከአንድ በላይ የሆነ የስራ መስክ" ማለት ራሱን የቻለ የንግድ ስራ ፈቃድ የሚሰጠው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ነው።"

7/ For purposes of this Article **"More than one Sector"** means more than one business activity for which separate business license is issued."

፲፰) የደንቡ አንቀጽ ፶፱ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፹፫ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፹፫ ተተክቷል፡-

18) Article 59 or renumbered Article 83 is deleted and replaced by the following new Article 83;

"፹፫. <u>በደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሚያዝ የሂሳብ መዝገብና ሰነድ</u>

"83. <u>Books of Account and Documents Maintained by Category "B" Taxpayers</u>

፩/ ማንኛውም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ በአዋጁ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሐ) መሰረት በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ ከወሰነ ይህንኑ የግብር ዓመቱ ከመጀመሩ ከሶስት ወር በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

1/ A Category "B" taxpayer who elects under Article 50 Sub Article (4) of Paragraph (c) of the Proclamation to maintain books of account shall notify the Tax Authority Three months before the beginning of the tax year.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ የሚይዘው የሂሳብ መዝገብ በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟላ መሆን አለበት።

2/ A taxpayer who voluntarily wishes to maintain books of account in accordance with Sub Article (1) of this Article shall maintain books of account that satisfy the requirements of the Proclamation.

CamScanner

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የታክስ ባለስልጣኑን ያስታወቀ ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱን የሂሳብ መዝገብ ሳይዝ የቀረ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣለው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል።

3/ A taxpayer who has notified the Tax Authority of their intention to maintain books of account in accordance with Sub-Article (1) of this Article, but fails to maintain the books of account for the tax year, shall be subject to the penalty imposed for failure to maintain records under the Tax Administration Proclamation.

፬/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ሰራተኛ የሚቀጥር ከሆነ ለሰራተኛው የሚከፍለውን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እና ከዚሁ ገቢ ላይ ተቀንሶ የሚቀረውን ማንኛውንም ግብር የሚያሳይ ሰነድ መያዝ አለበት።

4/ A Category "B' taxpayer, who hires employees, shall maintain a record showing the salary paid to such employees and the tax withheld.

፭/ በደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት የሚመደብ ማንኛውም ግብር ከፋይ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር ፪ ሚሊዮን ብር (ሁለት ሚሊዮን ብር) በታች ሆኖ፤ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበትን የሙያ ስራ እና በጠቅላላ ገቢ ላይ ተመስርቶ ግብር የሚከፈልበትን ሌላ የንግድ ስራ አጣምሮ የሚያከናውን ከሆነ፣ የሂሳብ መዝገብ መያዝ የሚኖርበት በአዋጁ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ለተጣለበት የሙያ አገልግሎት ዘርፍ ብቻ ይሆናል።"

5/ Any taxpayer categorized as a Category "B" taxpayer whose annual gross income is below Birr 2,000,000 (Two Million Birr), and who concurrently engages in both a professional activity subject to a mandatory book-keeping obligation and another business activity taxed on a gross income basis, shall only be required to maintain books of account for the professional service sector upon which the book-keeping obligation is imposed pursuant to the Proclamation.

፲፱) የደንቡ አንቀጽ ፷ ወይም የተሸጋሸገው አንቀጽ ፹፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፹፬ ተተክቷል፡-

19) Article 60 or renumbered Article 84 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 84:

“፹፬. የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፹፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተደነገገው መሰረት የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች በ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የግብር ዘመን በየሩብ ዓመቱ ሊከፍሉት የሚገባው ፳፭ በመቶ (ሃያ አምስት በመቶ) ግብር የሚሰላው የተርንኦቨር ታክስን ሳይጨምር ለ፪ሺ፲፯ ዓ.ም የግብር ዘመን የከፈሉትን የንግድ ትርፍ ግብር መሰረት በማድረግ ይሆናል።

፪/ የደረጃ “ለ” ግብር ከፋይ በአዋጁ አንቀጽ ፶ ስር ባለው ሰንጠረዥ መሰረት የሚከፍለው ግብር የሚሰላው ገቢው በጨመረ ቁጥር እያደገ በሚሄደው የማስከፈያ መጣኔ መሰረት የግብር ከፋዩ አጠቃላይ ገቢ በእያንዳንዱ እርከን ስር ተከፋፍሎ ነው።

፫/ የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች የገቢ ግብር ስሌት በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት ይከናወናል።

ዓመታዊ ጠቅላላ ሽያጭ (በብር)	ተፈጻሚ ምጣኔ (በመቶኛ)	ቅናሽ (በብር)
0 — 100,000	2%	0
100,001 — 500,000	3%	1,000
500,001 — 1,000,000	5%	11,000
1,000,001—1,500,000	7%	31,000
1,500,001 — ከ 2,000,000 በታች	9%	61,000

“84. Payment of Tax by “Category B” Taxpayers

1/ As provided under Article 89 Sub-Article (4) of the Proclamation the advance tax of 25% (Twenty Five percent) payable by Category “B” taxpayers in every quarter of the 2025/26 tax year shall be calculated based on the business profit tax paid in 2024/2025 excluding the turnover tax.

2/ Pursuant to the schedule under Article 50 of the Proclamation, the tax payable by Category “B” taxpayer shall be calculated on a progressive rate basis, wherein the total income of the taxpayer is allocated across each respective tax bracket.

3/ The income tax calculation for Category “B” taxpayers shall be in accordance with the following table.

Annual Gross Sales (in Birr)	Applic-able Rate (%)	Deductible (in Birr)
0 – 100,000	**2%**	0
100,001 – 500,000	**3%**	**1,000**
500,001 – 1,000,000	**5%**	**11,000**
1,000,001 –1,500,000	**7%**	**31,000**
1,500,001 – Below 2,000,000	**9%**	**61,000**

CamScanner

፳) ከደንቡ አንቀጽ ፷ ወይም ከተሸጋሸገው አንቀጽ ፹፬ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፹፭፣ ፹፮፣ ፹፯፣ እና ፹፰ ተጨምረዋል፦

"፹፭. <u>በደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በየሩብ ዓመቱ የሚከፈል ግብር የጊዜ ሰሌዳ</u>

፩/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በአዋጁ አንቀጽ ፹፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት በየሩብ ዓመቱ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው የጊዜ ሰሌዳ ይሆናል፦

ሀ) "የሒሳብ ጊዜያቸው በሰኔ ወር የሚያልቅና ሪፖርታቸውን እስከ ጥቅምት ወር መጨረሻ ድረስ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ከጥቅምት ወር ጀምሮ ከሚቆጠር የሶስት ወር ጊዜ በኋላ ማለትም በጥር፣ ሚያዝያ እና ሀምሌ ወራት የየሶስት ወሩን የቅድሚያ ግብር፣ እስከ ጥቅምት ወር መጨረሻ የአመቱን ግብር አጠቃለው ይከፍላሉ።።

ለ) የሂሳብ ሪፖርታቸውን ከሀምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ሐምሌ ፴ ቀን አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች የሀምሌ ወር የሶስት ወር ቅድመ ክፍያ የማይመለከታቸው ሲሆን በሚመጡበት ጊዜ እስከ ሐምሌ መጨረሻ የአመቱን ግብር አጠቃልለው መክፈል ይችላሉ።

ሐ) "የሒሳብ ጊዜያቸው እ.ኤ.አ. በዲሴምበር ወር የሚያልቅና ሪፖርታቸውን እ.ኤ.አ. እስከ ኤፕሪል ወር መጨረሻ ድረስ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች እ.ኤ.አ ከኤፕሪል ወር ጀምሮ የሚቆጠር የሶስት ወር ጊዜ በኋላ ማለትም ጁላይ፣ ኦክቶበር እና ጃንዋሪ ወራት የየሶስት ወሩን የቅድሚያ ግብር፣ እስከ ኤፕሪል ወር መጨረሻ የአመቱን ግብር አጠቃለው ይከፍላሉ።።

20) The following Articles 85, 86, 87, and 88 are added after Article 60 or renumbered Article 84:

"85. <u>Quarterly Advance Payments made by Category "A" Taxpayers</u>

1/ "Category 'A' taxpayers shall pay tax on a quarterly basis in accordance with Article 89 Sub-Article (2) of the Proclamation, pursuant to the following schedule:":

a) Taxpayers whose accounting period ends in June and who submit their reports by the end of October shall pay quarterly advance taxes every three months starting from October, which is in January, April, and July, and shall settle their total annual tax by the end of October.

b) Taxpayers who declare and pay their tax reports between July 1 and July 30 are not required to make the July quarterly advance payment; they may instead settle their total annual tax by the end of July upon submission.

c) Taxpayers whose accounting period ends in December and who submit their reports by the end of April shall pay quarterly advance taxes every three months starting from April, which is in July, October, and January, and shall settle their total annual tax by the end of April.

CamScanner

መ) የሂሳብ ሪፖርታቸውን እስከ ጃንዋሪ ወር መጨረሻ ቀን ድረስ አጠቃለው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች የጃንዋሪ ወር የሶስት ወር ቅድመ ክፍያ የማይመለከታቸው ሆነው እስከ ጃንዋሪ መጨረሻ የአመቱን ግብር አጠቃለው መክፈል ይችላሉ።

ሠ) የሂሳብ ሪፖርታቸውን በሌላ የጊዜ አቆጣጠር የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች በተመሳሳይ የሂሳብ ሪፖርታቸውን ከሚያቀርቡበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ከሚቆጠር የሶስት ወር ጊዜ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የየሶስት ወሩን የቅድሚያ ግብር፣ እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወር መጨረሻ የአመቱን ግብር አጠቃለው ይከፍላሉ።

ረ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፌደል ተራ (ሠ) ድንጋጌ ቢኖርም የሂሳብ ሪፖርት በሚቀርብበት የመጀመሪያ ወር አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች የሶስተኛው ወር የየሶስት ወር የቅድመ ክፍያ የማይመለከታቸው ሆኖ በሚመጡበት ጊዜ የአመቱን ግብር አጠቃለው መክፈል ይችላሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም የገቢዎች ሚኒስቴር በየሶስት ወሩ የሚከፈለውን የቅድሚያ ግብር የጊዜ ሰሌዳ የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፹፮. <u>በየሩብ ዓመት የሚከፈል ግብር የስሌት መሰረት</u>

፩/ በየሩብ ዓመቱ ለሚከፈለው ግብር መሰረት የሚሆነው በአዋጁ አንቀጽ ፹፱ በተደነገገው መሰረት ግብር ከፋዩ ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈለው ግብር ነው።

d) Taxpayers who settle their total tax reports by the end of January are not required to make the January quarterly advance payment and may settle their total annual tax by the end of January.

e) Taxpayers who submit their reports according to any other calendar shall pay quarterly advance taxes within one month following every three-month period, starting from the month following their reporting deadline, and shall settle their total annual tax at the end of the month in which they submit their reporting.

f) Notwithstanding the provisions of paragraph (e) of this sub-article, taxpayers who declare and pay in the first month of the reporting period are not required to make the third quarterly advance payment; they may settle their total annual tax at the time of reporting.

2/ Notwithstanding the provisions of this Article, the Ministry of Revenue may issue a directive prescribing the calendar for quarterly payments.

86. <u>Calculation of Quarterly Payments</u>

1/ As provided under Article 89 of the Proclamation the base for calculation of the advance tax payable quarterly shall be the tax paid in the preceding tax year.

CamScanner

፪/ ግብር ከፋዩ ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት ባለው ያለፈው የግብር ዓመት ኪሳራ ወይም የስራ እንቅስቃሴ ያልነበረው መሆኑን በመግለጽ ያስታወቀ ከሆነ በየሩብ ዓመቱ ለሚከፈለው ግብር መሰረት የሚሆነው ግብር የከፈለበት የመጨረሻው ዓመት ይሆናል።

2/ Where the taxpayer declared a loss or nil income in the preceding tax year the base for the quarterly advance payment shall be the tax paid in the most recent tax year in which tax was paid.

፫/ ግብር ከፋዩ በማስታወቅ የከፈለው እና በታክስ ባለስልጣኑ በተጠየቀው መሰረት በልዩነት እንዲከፍል የተደረገው ግብር ካለ በየሩብ አመቱ ለሚከፈለው ግብር መሰረት የሚሆነው የሁለቱ ድምር ይሆናል። ሆኖም የታክስ ባለስልጣኑ በጠየቀው መሰረት በልዩነት እንዲከፈል የተደረገው ግብር ላይ የሚከፈሉ ወለድ እና ቅጣቶች ታሳቢ አይደረጉም።

3/ If in the preceding year tax paid is paid both on the declaration of the taxpayer and on the difference requested by the Tax Authority the base for the advance payment shall be the total of the two sums. However, interest and penalties payable on the tax difference found out by the Tax Authority shall not be the basis for the advance tax payment.

፹፯. <u>በየሩብ ዓመቱ ከሚከፈለው ግብር ላይ ተቀናሽ ሂሳብ</u>

87. <u>Deductibles from the Advance Tax Payable</u>

፩/ በየሩብ ዓመቱ ሊከፈል የሚገባው የቅድሚያ ግብር በሚሰላበት ጊዜ ባለፈው ሩብ ዓመት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የቀረው ግብር እንዲሁም ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የተከፈለ የቅድሚያ ገቢ ግብር ተቀናሽ ይደረጋል።

1/ When calculating the advance tax payable in every quarter the withholding tax paid as well the advance tax paid on goods imported by the taxpayer in the quarter shall be deducted.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ግብር ከፋዩ ባለፈው ሩብ ዓመት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የቀረውን እንዲሁም ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የተከፈለውን የቅድሚያ ግብር በዚያው ሩብ ዓመት ተቀናሽ ካላደረገ በተከታዮቹ ሩብ ዓመታት ወይም የግብር ዓመቱ የተጠቃለለ የሂሳብ መዝገብ በሚቀርብበት ወቅት ተቀናሽ ለማድረግ ይችላል።

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, if a taxpayer fails to deduct tax withheld from payments or advance tax paid on imported goods during the same quarter in which they were incurred, the taxpayer may deduct such amounts in subsequent quarters or at the time the consolidated books of account for the tax year are submitted.

CamScanner

፹፰. የታክስ ማበረታቻ ተጠቃሚ የሆኑ ባለሃብቶች

፩/ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር ፭፻፹፮/፪ሺ፲፭ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም ከግብር ነጻ የመሆን እፎይታ የተሰጣቸው ባለሃብቶች ማበረታቻው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አማራጭ አነስተኛ ግብር እንዲከፍሉ አይገደዱም።

፪/ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቁጥር ፭፻፹፮/፪ሺ፲፭ መሰረት ከመደበኛው ባነሰ የማስከፈያ መጣኔ ግብር እንዲከፍሉ ማበረታቻ የተሰጣቸው ባለሃብቶች ሊከፍሉት የሚገባው አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚሰላው ከመደበኛው ካነሰው የማስከፈያ መጣኔ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ይሆናል።

፫/ ከግብር ነጻ የመሆን ማበረታቻ የተሰጣቸው ባለሃብቶች አማራጭ አነስተኛ ግብር እንዲከፍሉ አይገደዱም።

፳፩) የደንቡ አንቀጽ ፷፫ ወይም በተሻሻለው አንቀጽ ፺፪ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፺፪ ተተክቷል፡፡

“፺፪. <u>ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚያዝ ግብር</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፺፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ማንኛውም ግብር ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ ግብርን ቀንሶ የመያዝ ኃላፊነት ላለበት ሰው የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

88. <u>Taxpayers with Tax Incentives</u>

1/ Taxpayers issued with investment permit or acquired tax holiday prior to the entry in to force of the Investment Incentives Regulations No. 586/2026 shall not be liable to pay Minimum Alternative Tax until the end of the incentive period.

2/ Taxpayers that are accorded with reduced rate in accordance with the Investment Incentives Regulations No. 586 /2026 shall pay the Minimum Alternative Tax in proportion to the reduced rate

3/ Investors granted profit tax exempt incentives shall not be required to pay Minimum Alternative Tax.”

21) Article 63 of the Regulation or the renumbered Article 92 is hereby deleted and replaced by the following new Article 92:

“92. <u>Withholding of Tax from Payments</u>

1/ In accordance with Article 97 Sub-Article (4) of the Proclamation, any taxpayer shall have the obligation to provide their Taxpayer Identification Number (TIN) and a valid business license to the person obligated to withhold tax.

CamScanner

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ተቀናሽ በሚደረግበት ጊዜ ግለሰብ ቤት አከራዮች እና ዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ ሲሆን፤ በጥብቅና ስራ ላይ የተሰማሩ የግብር ከፋዮች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የጥብቅና ስራ ፈቃድ ማቅረብ አለባቸው።"

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the documentation required to be presented at the time of tax withholding shall be the Taxpayer Identification Number (TIN) only in the case of individual lessors of buildings and digital content creators, and both the Taxpayer Identification Number and a professional advocacy license in the case of taxpayers engaged in the practice of law."

፳፪) ከደንቡ አንቀጽ ፷፰ ወይም በተሻሻለው አንቀጽ ፺፯ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፺፰ ተጨምሯል፡፡

"፺፰. <u>ለንግድ ትርፍ ግብር ተመላሽ ስለሚያዝ ገንዘብ</u>

የታክሱ ባለሥልጣን ለንግድ ትርፍ ግብር ተመላሽ ክፍያ እንዲያውለው ከጠቅላላ የንግድ ትርፍ ግብር ተሰብሳቢ ገንዘብ ላይ ተቀናሽ አድርጎ የሚይዘው መቶኛ መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡"

22) Following Article 68 or the amended Article 97 of the Regulation, the following new Article 98 is added:

98. <u>Retention of Funds for Business Profit Tax Refunds</u>

The percentage of total collected business profit tax to be withheld by the Tax Authority for business profit tax refunds shall be determined by a directive issued by the Ministry."

፳፫) ከአንቀጽ ፸፯ ጀምሮ እስከ አንቀጽ ፻፩ ድረስ ያሉት የነባሩ ደንብ ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፸፰ እስከ ፺፱ በሚል ተስተካክለዋል፡፡

23) Articles 27 to 71 of the amended Regulation are renumbered consecutively as Articles 28 to 99.

፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በደንቡ አንቀጽ ፶፬ ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ ፶፯ የተደነገገው ቢኖርም፤ ይህ ደንብ ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ከውጭ ምንዛሪ ጥቅም ጋር እስኪካካስ ድረስ በግብር ከፋዩ በተለየ ተንከባላይ ሂሳብ ተይዞ የቆየ የውጭ ምንዛሪ ኪሣራ፡-

3. <u>Transitional Provision</u>

Notwithstanding the provisions of Article 44 or the renumbered Article 47 of the Regulation, foreign exchange losses accumulated before the entry in to force of this Regulation and held in a separate suspense account by the taxpayer awaiting offset against foreign exchange gains, shall be treated as follows:

CamScanner

ሀ) ከካፒታል ሀብት ግብይት ጋር የማይያያዝ ከሆነ፣ ኪሣራው በሚቀጥሉት ፲ (አስር) ዓመታት ውስጥ በእኩል መጠን ተከፋፍሎ በየግብር ዓመቱ በወጪነት ይያዛል፤

ለ) ከካፒታል ሀብት ግብይት (የካፒታል ንብረት ማፍራት) ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ በህጉ ለንብረቱ በተፈቀደው የእርጅና ቅናሽ መሠረት ከንብረቱ ዋጋ ላይ ተደምሮ በየግብር ዓመቱ በወጪነት እንዲያዝ ይደረጋል።

a) If not related to capital asset transactions, the loss shall be deducted as an expense in equal portions over the subsequent Ten (10) tax years;

b) If related to capital asset transactions (capital asset acquisition), the loss shall be added to the asset's cost basis and deducted as an expense annually in accordance with the depreciation allowance permitted by law.

፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

4. <u>Effective Date</u>

፩/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል (መ) ድንጋጌ ያልተከፈለ ግብርን በተመለከተ በሚኒስቴሩ ውሳኔ የተካተቱትን የግብር ዓይነቶችና የግብር ዘመናትን ጨምሮ ሚኒስቴሩ ጊዜያዊ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

1/ The provision of Article 78 Sub-Article (1) Paragraph (d) of this Regulation shall be effective as of the date on which the Ministry issues a temporary decision, including the tax types and tax periods covered under the decision of the Ministry.

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ያልተከፈሉ የግብር ዕዳዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደልተራ (ሐ) በተደነገገው መሠረት እልባት የሚያገኙ ሲሆን፤ በዚህ መሠረት እልባት በሚያገኙ ማናቸውም ባልተከፈሉ ወይም በሂደት ላይ ባሉ የግብር ግዴታዎች ላይ በግብር ከፋዩ ላይ ወለድና ቅጣት አይታሰብም።

2/ Any unpaid tax liabilities under Article 12 of these Regulations shall be resolved in accordance with the provisions of Article 7 Sub-Article (1) Paragraph (c) hereof; provided that no interest or penalties shall be assessed against the taxpayer on any unpaid or pending tax obligations so resolved.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች ደንቡ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸኑ ይሆናሉ።

3/ Subject to Sub-Article (1) of this Article, the other provisions of this Regulation shall enter into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፱ ዓ.ም.

ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

Done at Addis Ababa, on this 28th Day of October, 2026

ABIY AHMED (DR.)
PRIME MINISTER OF THE
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC
OF ETHIOPIA

CamScanner